የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ ታህሳስ ፴ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No 8
ADDIS ABABA 8TH January, 2021

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴/፪ሺ፲፫ ዓ.ም
በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በራሽያ ፌዴሬሽን መንግሥት መካከል የኒውክለር ኃይልን ለሠላማዊ ዓላማ ለማዋል የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ .ገጽ ፲፪ሺ፱፻፵

**Content**

Proclamation No. 1230/2021
Agreement on Cooperation in the Field of the Use of Nuclear Energy for Peaceful Purposes between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Russian Federation Ratification Proclamation ……......................................................Page 12940

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴/፪ሺ፲፫**

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በራሺያ ፌዴሬሽን መንግስት መካከል የኒውክለር ኃይልን ለሠላማዊ ዓላማ ለማዋል የተደረገ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በራሽያ ፌደሬሽን መንግሥት መካከል የኒውክለር ኃይልን ለሠላማዊ ዓላማ ለማዋል የተደረገው ስምምነት ጥቅምት፲፫ ቀን ፪ሺ.፲፩ ዓ.ም በሞስኮ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕዳር ፳፬ ቀን ፪ሺ.፲፫ ዓ.ም ባካሄደው ፭ኛ መደበኛ ስብሰባው ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**PROCLAMATION NO. 1230/2021**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE RUSSIAN FEDERATION ON COOPERATION IN THE FIELD OF THE USE OF NUCLEAR ENERGY FOR PEACEFUL PURPOSES**

WHEREAS, the Agreement on Cooperation in the Field of the Use of Nuclear Energy for peaceful Purposes between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Russian Federation was signed in Moscow on the 23rd day of October, 2019;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its 5th regular session held on 3rd day of December, 2020;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby Proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በራሽያ ፌዴሬሽን መንግሥት መካከል የኒውክለር ኃይልን ለሠላማዊ ዓላማ ለማዋል የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴/፪ሺ፲፫ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በራሽያ ፌዴሬሽን መንግሥት መካከል የኒውክለር ኃይልን ለሠላማዊ ዓላማ ለማዋል ጥቅምት፲፫ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም በሞሰኮ ከተማ የተፈረመው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>ፈጻሚ አካል</u>**

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ የጨረራ መከላከል ባለሥልጣን አግባብነት ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቷቸዋል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፴ ቀን ፪ሺ፲፫ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as ‘’Agreement on Cooperation in the Field of the Use of Nuclear Energy for Peaceful Purposes between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Russian Federation Ratification Proclamation No.1230/2021.’’

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Agreement of Cooperation in the Field of the Use of Nuclear Energy for Peaceful Purposes between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Russian Federation signed in Moscow on the 23rd day of October, 2019 is hereby ratified.

**3. <u>Implementing Organ</u>**

The Ministry of Innovation and Technology and the Ethiopian Radiation Prevention Authority are hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon publication in the *Federal Negarit Gazettee*.

**Done at Addis Ababa, on this 8th day of January, 2021.**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**